MIDROC Newsletter

Special Issue # 55

A BI-MONTHLY PUBLICATION OF THE OFFICE OF THE CHIEF EXECUTIVE OFFICER

This Newsletter provides customers, employees, suppliers, shareholders and the community at large with current information on major performance and other activities of the companies under the leadership of the CEO

Special Issue # 55 May 2018

# የእናት ቀን አከባበር በሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ



*ዶ/ር አረጋ ይርዳው የእናት ቀን አከባበርን አስመልክተው ገለጻ ሲያደርጉ*

የሀገር ወዳዱ የሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል-አሙዲ ሀብት የሆነው በሀገሪትዋ ክልሎች በዘርፈ ብዙ የሥራ መስኮች ማለትም በማዕድን፣ በግብርና፣ በሪል እስቴት፣ በአየርና በየብስ ትራንስፖርት፣ በአስጎብኝነት፣ በብረትና ፕላስቲክ ምርት፣ በንግድ፣ በትምህርትና በጤና አገልግሎቶች የተሠማራውና በቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር/ፕሬዚዳንት ዶ/ር አረጋ ይርዳው የበላይ አመራር ሥር ያለው ሃያ አምስት ኩባንያዎች አባል የሆኑበት ሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ለሰባት ሺህ ያህል ዜጐች የሥራ ዕድል በመፍጠርና ከፍተኛ ታክስና ግብር ለመንግሥት በማስገባት የታወቀ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ቴክኖሎጂ ግሩፑ ሠራተኞቹን በሚመለከት ልዩ ልዩ ዝግጅቶች (events) እንዲኖሩና ባህል ሆነው ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኙ ሲሆን በዚህም ረገድ ‹‹የቤተሰብ ቀን›› ‹‹የስፖርት ውድድር ቀን›› የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰራችን ዶ/ር አረጋ ይርዳው አነሳሽነት በቴክኖሎጂ ግሩፑ ኩባንያዎች ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን (March 8) እና የእናት ቀን (Mother's Day) የማክበሩ ሁኔታ ተጀምሯል፡፡

የእናት ቀን አከባበር ባለፈው ግንቦት 4 ቀን 2009 ዓ.ም ዶ/ር አረጋ ይርዳው፣ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በተገኙበት በሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ በመቻሬ ኮርፖሬት ሴንተር አዳራሽ በደመቀ ሥነ ሥርዓት ተከብሯል፡፡

ከዚሁ እናት ቀን አከባበር ጋር በተያያዘ ባለፈው ዓመት በተገባው ቃል መሠረት ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ፈቃድ በማግኘት በሀገራችን ታዋቂ ለነበረችው ‹‹የእናት ውለታዋ›› እያለች ላዜመችው ብዙነሽ በቀለ የመካነ መቃብሯ ሀውልት በቴክኖሎጂ ግሩፑ ማኔጅመንትና ሠራተኞች ስም እንዲታደስ ተደርጓል፡፡ የዚህ ሀውልት እድሳት ሥራ የተከናወነው የቴክኖሎጂ ግሩፑ አባል በሆነው የሁዳ ሪል እስቴት ኃ.የተ.የግል ኩባንያ ነው፡፡

በዓለም የተለያዩ ሀገሮች በወርሀ ግንቦት የእናትን ቀን፣ እናቶችን በማወደስ፣ ምሥጋና በማቅረብና በመሳሰሉት

የማክበር ባህል የተለመደ ነው፡፡ ይህ ባህል በሀገራችን ገና በብሔራዊ ደረጃ መከበር አልጀመረም፡፡ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር/ፕሬዚዳንት ዶ/ር አረጋ የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ኩባንያዎች ሠራተኞች የእናትን ቀን በሥራ ቦታ እንዲከበር ማድረጋቸው፣ በዋናነት ለሴቶች የሚሰጡትን ክብር የሚያሳይ ሲሆን ሌላው ደግሞ በዚህ ጉዳይ ቴክኖሎጂ ግሩፑ ለሌሎች መሠል ተቋማት አርአያ እንዲሆን ነው ማለት ይቻላል፡፡

ባለፈው ዓመት የእናት ቀን አከባበር በቴክኖሎጂ ግሩፑ ባህል ሆኖ እንዲቀጥል በተወሰነው መሠረት ዘንድሮም በዓለም በተለያዩ ሀገሮች ቀኑ ሜይ 13, 2018 የሚከበር ሲሆን ቀኑ እሁድ ላይ በመዋሉ የቴክኖሎጂ ግሩፑ ሠራተኞች በዚሁ ዕለት በየቤታቸው የእናትን ቀን የሚያከብሩ ሆኖ ከወዲሁ ግንቦት 3 ቀን 2010 ዓ.ም ሠራተኞች በአንድ ላይ ሆነው በመቻሬ ኮርፖሬት ሴንተር ቀኑን ለማክበር ተሰባስበዋል፡፡



*የብዙነሽ በቀለ መካነ መቃብር የቀድሞ ሀውልት*




*የብዙነሽ በቀለ መካነ መቃብር አዲሱሀውልት*

*ድምፃዊት ብዙነሽ በቀለ በሐረርጌ ክ/ሀገር ሐረር ካፈራቻቸው ታዋቂ የሀገራችን የጥበብ ሰው ናት፡፡ ድምፃዊቷ አብዛኛውን የሙዚቃ ሥራዎቿን በክብር ዘበኛ ኦርኬስትራ ጋር ሠርታለች አልፎ አልፎም ከተለያዩ ኦርኬስራዎች ጋር መሥራቷ ይታወሳል፡፡ የብዙነሽ በቀለ የሙዚቃ ህይወት የሚጀምረው ገና ከአንደኛ ደረጃ ትህምርቷ ነው፡፡ ገና ብዙ ባልተቆጠረው ዕድሜዋ በክብር ዘበኛ ጠቅላይ መመሪያ የሬዲዮ ጣቢያ እንደቀጠራት ይነገራል፡፡ የዚያን ጊዜ የሥራ ድርሻዋም ድምፃዊነት ነበር፡፡ በተለይ በየሳምንቱ ሐሙስ ሐሙስ በጃንሜዳ ይታይ በነበረው የሙዚቃ ዝግጅት ላይ ድምፃዊቷ ፋና ወጊነቷን ያስመሰከረችበት ጥበባዊ ጉዞዋ ነበር፡፡ የክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ የሬዲዮ ጣቢያ በጊዜው በኢትዮጵያ ሙዚቃ ዕድገት ለብዙ ድምፃዊያን መሰረት የጣለና ለድምፃዊት ብዙነሽ በቀለ ደግሞ ግንባታንም ያሳመረተም ነበር፡፡የአገር ባህል ዘፈኖችንና ዘመናዊ ዘፈኖችን ከተለያዩ አገራዊ ማህበራዊና ወቅታዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ የየትኛወም ትውልድ ልብ መዝገብ ውስጥ ያለችዋ ድምፃዊት ብዙነሽ በቀለ የዜማና የግጥም ሥራዎቿን በሙዚቃ ያዋሃዱላትን የተለያዩ ኦርኬስትራዎች ሲጠቀሱ በየጊዜው የነበሩት ሥመ ጥር የዜማና ግጥም ደራሲዎች ከብዙነሽ ጋር በየዘመኑ መነሳታቸውን ልብ ማለት ያሻል፡፡ እናም ብዙነሽ ከተለያዩ የዜማና የግጥም ደራሲዎች ጋር ሠርታለች፡፡ ድምፃዊት ብዙነሽ በቀለ በዘመኗ የሚስተካከላት እንስት ድምጻዊ አልነበረም፡፡ የመድረክ አያያዟና እንቅስቃሴዋን የሚያስታውሱ ሁሉ ኮኮብነቷን ይመሰክሩላታል፡፡ ብዙነሽ በቀለ ከሙዚቃ ህይወቷ በሞት እስከተለየችበት ጊዜ ድረስ ለሙያዋ ቀዳሚና አክባሪ፣ ለሙያ ባልደረቦችዋና ለሀገሯ ህዝብ ፍቅር ያላት ምርጥ የጥበብ ሰው ነበረች፡፡*

# መልካም የእናት ቀን!!

*ፍሬ ስትበላ ማን ዛፉን እንደተከለ፤ ውሃ ስትጠጣ ደግሞ ማን ጉድጓዱን እንደቆፈረ አስብ*

*ዶ/ር አረጋ ይርዳው*
*የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ቺፍ ኤግዚኩቲቭ ኦፊሰር/ፕሬዚደንት*

እኔ ሁል ግዜ ንግርር ሳደርግ ስለ ግዑዝ ነገር ሳይሆን ስለ ሰው፣ ስለ ስለውስብስብ ሃሣብ ሳይሆን ስለቀላል ነገር፣ ስለማስረዳት ሳይሆን ስለመረዳት፣ እንደሆነ አዉቃለሁ:: እኔ ከእናቴ የተማርኩት ሰዋዊ የሆነ ማንነቴን የሚያሳይ ሰብዓዊነት መሆኑን ደጋግሜ ተናግሪያሉ:: "እኔ የእናቴ ልጅ ነኝ" እናቴ የመገኘቴ ምንጭ፣ እናቴ በጥንካሬ የመኖሬ ምክንያት በመሆኗ እኮራለሁ::

ብዙ እናቶች የትላንት ስሜ፣ ስራዬ፣ ክብሬ ሳይሉ እራሳቸውን አዋርደውና ዝቅ አድርገው ደምግባትና ወዛቸውን ለግሰው እየራባቸው አጥግበው የት እንዳደረሱ እናውቃለን:: በመሆኑም ስም ሳይኖራቸው ገናና ስም እንዲኖረን፣ ህልምና ራዕያቸው በጠቅላላ የኛ ምኞት ሆኖባቸው ለዚህ ላበቁን እናቶቻችን በአጠቃላይ ክብር ይሁን››

በአሁኑ ወቅት የሀገር ባለውለታ እና የቁርጥ ቀን ልጅ የሆኑት እና ዘወትር በልባችን ያሉትን በተለይም እኔ ሀገራዊ ፋይዳ ባለቸው ቦታዎች ላይ በእንግድነት ስገኝ ወንድሜ ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አላሙዲ አብሮኝ በኖረ የምልባቸው ቀኖች መኖራቸው እውነት ነው:: ሊቀመንበራችን በዚህ ታሪካዊ ወቅት ከእኛጋር ቢገኝ እንዴት ደስ ባለን ሆኖም በርዕሴ እንደገለጸኩት ፍሬ ስትበላ ማን ዛፉን እንደተከለ፤ ውሃ ስትጠጣ ደግሞ ማን ጉድጓዱን እንደቆፈረ አስብ ነውና የመሰባሰባችን ምክንያት በመሆኑ ሁላችንም በጸሎታችን እንድናስበው እጠይቃለሁ::

ከሰማይ ዝናብ ቢዘንብ ምድሩን ካላራሰው ና የተዘራውንም እህል እንዲበቅል ካላደረገው ጉርምርምታውን ብቻ አሰምቶ ቢቀር በምድር ላይ አንዳች ጥቅም ሊገኝ አይችልም:: በቅርቡ የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ 25 ኩባንያዎች ከኢትዮ ሱማሌ ክልል ለተፈናቀሉ ወገኖቼ እናቶቼ በቢሾፍቱ ከተማ የገነባውን የ121 ቤቶች ቁልፍ በዕለተ ቅዳሜ መጋቢት 1ቀን 2010 ዓ.ም ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለማስረከብ ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር በተገኘሁበት ወቅት ከክልሉ መሪዎች የሰማሁት እውነተኛ ምስጋና ልቤን ስለነካው በዚህ በእናት ቀን ለማስታወስ ግድ ይለኛል::

በተለይ በዕለቱ የገንዘብና የኢኮኖሚ ቢሮ ኃላፊው የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አል- አሙዲ ለተፈናቃይ ወገኖች የ40 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ለወገኖቻችን የሰጡት የተስፋ ቃል እጅግ የሚያበረታታ እንደነበር እና በነበር ብቻ እንዳልቀረ ከታላቅ ምስጋና ጋር ሲናገሩ፤ የተግባር ምዕራፉ ከቃል የበለጠ የመሥራት ኃላፊነት አሰደረብኝ::

"ይህ ማለት ግን ለተፈናቃይ ወገኖች በሚሊየን የሚቆጠር ገንዘብ አውጥተን ቤት መሥራታችን ሳይሆን ቁም ነገሩ፤ ይህንን ለመሥራት የኩባንያዎቻችን ሠራተኞች ከክልሉ ሕዝብ ጋር በመተባበር ሌት ተቀን በፍላጐት ለመሥራት ያደረጉት ርብርብ እና ውጤቱ ነው እርካታችን:: በዚህም የሊቀመንበራችንን የክብር ዶ/ር ሼህ ሙሐመድ ሁሴን አሊ አላሙዲን ቃል ማክበራችን በእጅጉ ያስደስተናል::

"እነዚህ እናቶች እና ቤተሰቦች ትልቅ ነገር ተደርጐላቸዋል ለማለት አልደፈርም፤ ምክንያቱም የተፈናቀሉት ከሞላ ቤት ንብረታቸው በመሆኑ፤ ነገር ግን ከአንዱ ምዕራፍ ወደ ሌላው ምዕራፍ እንዲሸጋገሩ የሚያደርገውን የማረፊያ ቤት ግንባታ አናጠናቀን፣ ተፈናቃዮቹን እራት በማብላት እና ለቁርሳቸው የሚሆነውንም በማዘጋጀት እንኳን ደህና መጣችሁ ብለናል::

የእናትነት መገለጫ ቃሉ ጥልቅ ነው:: እናትነት በልባችን ውስጥ ትልቁን ቦታ ይዞ እናገኘዋለን:: ዛሬ በሕይወት የሌሉት ድምጻዊያኑ ሻለቃ ወጋየሁ ደግነቱ እና ብዙነሽ በቀለ ሙዚቃ ውስጥ ካገነኗቸው ስራዎቻቸው መካከል ስለ እናት ያዜሟቸው ሙዚቃዎች ናቸው:: የናትነትን ርዕሰ ጉዳይ ይዘው ብቅ የሚሉ የጥበብ ውጤቶች የታዳሚን መንፈስና ቀልብ በቀላሉ የመቆጣጠር አቅማቸው ትልቅ ነው::

"እኔ የእናቴ ልጅ ነኝ" በተለይም የእናት ውለታዋ የሚለውን ዜማ አቀንቅና የማይረሳ ታሪክ ሠርታ ያለፈችው ብዙነሽ በቀለ "ብዙነሽ በቀለ ስለ እናት ውለታ ያዜመችው ዜማ ሲደመጥ የእናቶቻችንን ዉለታ እንድናስታውስ በዜማዋ ዘላለማዊ ሃውልት በልባችን ውስጥ ተክላ ከማለፏ ባሻገር እርሷም እናት ናትና እና ባለውለታ ስለሆነች ሁሌም እናስባት" በማለት ሐውልቷ እንዲታደስ እና ሥራዋን በእናቶች ቀን ለመዘከር በ2009 ዓ.ም የገባሁት ቃል በተግባር ተተርጉሟል::

"ሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ ምን ጊዜም የወንድሜን የሼህ ሙሐመድን ሁሴን አሊ አላሙዲንን አርአያነት ተከትሎ እንደሚሠራ እየገለጽኩ፤ መልካም የእናት ቀን ይሁንልን::

# ጠቅላይ ሚኒስትራችን ስለ እናት ምን አሉ?



## “እናቴ ከሌሎቹ ቅን የዋህ እና ጎበዝ ኢትዮጵያውያን እንደ አንዶቹ የምትቀጠር ናትና.... ”

*ክቡር የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 24 2010 ዓ.ም ካደረጉት ንግግር*

‹‹ውድ የኢትዮጵያ ሴቶች

በብዙ አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ኢትዮጵያን ገንብታችሁ፣ ታሪክ ሰርታችሁ፣ ትውልድ ቀርጻችሁ ዛሬ ላይ ደርሰናል:: በትግላችሁም የተሻለች ሃገር እንድትኖረን ብዙ መስዋዕትነት ከፍላችኋል:: ትግላችሁ የፍትህ ትግል ነው፣ ትግላችሁ ክቡር ትግል ነው፣ ትግላችሁ ትግላችን ነው:: መንግስት የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና በሃገራችን ሁለንተናዊ የእድገት ግስጋሴ ውስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ለማስቻል የተለያዩ ስራዎችን በመስራት ላይ የሚገኝ ቢሆንም አሁንም ከሰራነው ይልቅ ያልሰራናቸው ስራዎች እጅግ እንደሚበዙ እናምናለን:: በመሆኑም በቀጣይ የሃገራችን ሴቶች ተፈጥሮ እና ኑሮ የሰጧችሁን በረከቶች ተጠቅማችሁ ለሃገራችን እድገት እና ብልጽግና እንዲሁም ለፖለቲካችንም ስምረት አዎንታዊ ሚና እንደምትጫወቱ ተስፋዬ የላቀ ነው::

አገራዊ ማንነታችን ያለ እናንተ ያለ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ምንም ነው:: አገሪቷን የገነቡ፣ ያገለገሉ፣ ያቆሙ ሴቶችን እውቅና በመንፈግ ሀገራዊ ትንሳኤን ማረጋገጥ አይቻልም:: መንግስታችን ለሴቶች መብትና እኩልነት የሚቆመው፣ ለሴቶቻችን ውለታ ለመዋል ሳይሆን ለሁላችንም ብለን ነው:: ግማሽ አካሉን የረሳን ሀገር ሙሉ የሀገር ስዕል ይኖረው ዘንድ ከቶ እንደማይችልና ወደፊትም እንደማይራመድ መንግስት በውል ይገነዘባል:: በመሆኑም መንግስታችን ከዚህ ቀደም ከነበረው ፍጥነት እና የትግበራ ስኬት በላቀ መልኩ ለሴቶች ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት በቁርጠኝነት ይሰራል::

የሰባት ዓመት ልጅ እያለሁ እንዲህ ከፊታችሁ እንደምቆም የምታውቅ እና ይህንን ሩቅ ጥልቅ እና ረቂቅ ራእይ በውስጤ የተከለች፣ ያሳደገች እና ለፍሬ ያበቃች አንዲት ኢትዮጵያዊት እናት እንዳመሰግን በትህትና እጠይቃለሁ..... ይህች ሴት እምዬ ናት፤

እናቴ ከሌሎቹ ቅን የዋህ እና ጎበዝ ኢትዮጵያውያን እንደ አንዶቹ የምትቀጠር ናትና ቁሳዊ ሀብት ብቻ ሳይሆን አለማዊ እውቀትም የላትም:: በእናቴ ውስጥ ሁሉንም የኢትዮጵያ እናቶች ዋጋ እና ምሥጋና እንደመስጠት በመቁጠር ዛሬ በህይወት ካጠገቤ ባትኖርም ውዷ እናቴ ምሥጋናዬ ከዐፀደ ነፍስ ይደርሳት ዘንድ በብዙ ክብር ላመሰግናት እወዳለሁ::

ሌሎች ኢትዮጵያውያን እናቶቼ በልጆቻቸው የነገ ራእይ ላይ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው በመገንዘብ ነገ ለሚያጥፉት መልካም ፍሬ ዛሬ ላይ የሚዘሩት ዘር ዋና ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ለሚከፍሉት መስዋእትነት ያለኝን በምንም የማይተካ አድናቆት ምስጋና እና ክብር በብዙ ልባዊ ፍቅር ሳቀርብ በቀጣይም ልጆቻችን የዚህች ሀገር ህዳሴ እንዲረጋገጥ ዋና ተዋንያን መሆን እንዲችሉ እናታዊ አይተኬ ሚናችሁን እንድትወጡ አደራ በማለትም ጭምር ነው::

ሦስተኛ የሚስቶች ስኬት ሁለት-ሦስት ነው:: ሁለት ሲሆን፣ አንዱ የራሳቸው ሌላው የባላቸው:: ሦስት ሲሆን ደግሞ የልጆቻቸውም ይጨመርበታል:: አንዳንዴ ድል ስኬታቸው ከዚህም ይሻገራል:: የእናቴን ራእይ ተረክባ በብዙው የደገፈችኝና የእናቴ ምትክ የሆነችልኝ ውዷ ባለቤቴ ወ/ሮ ዝናሽ ታያቸው ከነዚህ ሚስቶች ተርታ ትመደባለችና እጅግ አድርጌ ላመሰግናት እወዳለሁ::በመጨረሻም ከትግል ጓዶቼ እና በዝለት ብርታት፤ በድካም ጊዜ ኃይል ከሆኑኝ የቅርብ-የሩቅ ወዳጆቼ ውጪ ዛሬ እኔ ከፊታችሁ መቆም ባልቻልኩ ነበር፤ ለሁላችሁም ከልብ የመነጨ ምሥጋና አቀርባለሁ::›› በማለት የሴቶች እና የእናቶች ታላቅነትን መስክረዋል::

# ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ስለ እናት ምን አሉ?



## “እኔ የእናቴ ልጅ ነኝ”

## ‹‹የእናት ቀን በሀገራችን በብሔራዊ ደረጃ የሚከበርበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፤ በኔ መሥሪያ ቤት ያደረግነውም ይኸው ነው፡፡

## “እኔ አምስት እናቶች አሉኝ”

*ክቡር ዶ/ር አረጋ ይርዳው የሚድሮክ ቴክኖሎጂ ግሩፕ*
*ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር/ፕሬዚደንት*
*ግንቦት 2008 ዓ.ም*
*የእናቶች ቀን ሲከበር ከተናገሩት*

«የእናቶች የበላይነት ያለባት ዓለም ውሎ አድሮም ቢሆን ትፈጠራለች!!!» “እኔ የእናቴ ልጅ ነኝ” ስለዚህ የእናት ውለታዋ የሚለውን ዜማ ስሰማ “ብዙነሽ በቀለ የእናቶቻችንን ውለታ እንድናስታውስ የሚያደርግ ዘላለማዊ ሃውልት በልባችን ውስጥ ተክላ ከማለፏ ባሻገር እርሷም እናት ናትና እና ባለውለታ ስለሆነች በሥራዋ እናስባት” ብለዋል፡፡ ከዚህም አኳያ ድምጻዊቷ ሐውልቷ እንዲታደስ እና የእናቶች ቀን በቴክኖሎጂ ግሩፑ ሠራተኞች እንደ ባህል እንዲከበር ሲኢኦአችን መወሰናቸው ስለእናት ያላቸው የከበረ አመለካከት ከአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ንግግር ጋር የተመሳሰለ እና ትክክለኛ ስብዕናን የሚገልጽ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ዶ/ር አረጋ በማያያዝም ‹‹ፈጣሪ ሲፈጥረን ለሴቶች አዳልቷል፡፡ መውለድ የሚባለውን ፀጋ ለነሱ ሰጣቸው፡፡ ሌሎች ሌላ ሊሉት ይችላሉ፤ እኔ ግን ቁምነገረኛ መሆናቸውን አውቆ መውለድ ለሚሉት ታላቅ ፀጋ መረጣቸው ነው የምለው፡፡ እኔ አምስት እናቶች አሉኝ፡፡ ሰው እንዴት ከአምስት እናት ይወለዳል ልትሉ ትችላላችሁ፡፡ ግን ለእኔ ይህ እውነት ነው የመጀመሪያዋ እናቴ ሀገሬ ናት፡፡ ሁለተኛዋ እናቴ ዘጠኝ ወር በማህፀኗ ይዛ የወለደችኝ፣ የደረቷን ጡት አጥብታ ያሳደገችኝ እናቴ ናት፡፡ እሷ አልተማረችም፤ እኔን ግን አስተምራ ለዚህ ደረጃ አብቅታኛለች፡፡ ሶስተኛዋ እናቴ የምላት ጥሩ ጥሩ ልጆችን የወለደችልኝ ባለቤቴ ነች፡፡ አራተኛዋ ደግሞ የአብራኬ ክፋይ ሴት ልጅ ነች፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ አምስተኛ እናቶች አሉኝ፡፡ እነሱ እነማን መሰሏችሁ በመሥሪያ ቤቴ ያሉ ሴቶች ናቸው፡፡

ዓለም እነኝህ እናቶች ባይኖሯት ኖሮ ብርቱ ችግር ውስጥ ትገባ ነበር፡፡ አሁንም አንድ ነገር ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ የእናቶች የበላይነት ያለባት ዓለም ውሎ አድሮም ቢሆን ትፈጠራለች፡፡ ያኔ አሁን የምናየው ግጭትና ትርምስ ተወግዶ ውብ ዓለም እናያለን፡፡ እናቶችን የምንረዳው ወደን አይደለም፡፡ የቆምነው በነሱ ስለሆነ ነው፡፡ የመጀመሪያ ልጇን ስትወልድኮ የሚኖራት ልጅ አንድ አይደለም፡፡ ሁለትነው፤ ባልም ራሱ ልጅ ነው፡፡

እናት ሁሉ ነገር መሆኗን እንዲሁም ሰባት የሥራ ድርሻ አላት ብሎ ማየት እንደሚቻል ለብራራ እወዳለሁ፣ የመጀመሪያው የሥራ ድርሻዋ ከማግባትዋ በፊት የምታደርገው ምርጫ፣ ሁለተኛው ወደ ትዳር ስትገባና ስትፀንስ፣ ሦስተኛው ልጅ ስታሳድግ፣ አራተኛው ልጇን ስታስተምር፣ አምስተኛው ተምሮ ሲጨረስ ሥራ ያገኝልኛል ብላ ስትጨነቅ፣ ስድስተኛ ልጇን ስትድር ልጇን ከዳረች በኋላም ስለ ልጇ ስትጨነቅ እና ሰባተኛ አያት ተብላ ስትጠራ የልጅ ልጅ ስታሳድግ ሲሆን በዚህ ሁሉ ሂደት እናት እራሷን ለቀጣይ ሥራ ዝግጁ ማድረጓ ልዩ ያደርጋታል ብለዋል፡፡ ‹‹የእናት ቀን በሀገራችን በብሔራዊ ደረጃ የሚከበርበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፤ በኔ መሥሪያ ቤት ያደረግነውም ይኸው ነው፡፡ ሴቶች በሥራ ቦታ ያስፈልጉናል፡፡ ለሀገራቸውም እድገት ለራሳቸውም ህይወት መሥራት አለባቸው፡፡ አሁን አሁን ደግሞ በቤት ሠራተኛ መቅጠር ከባድ እየሆነ መጥቷል፡፡ በዚህ ምክንያት እናቶች ወደ ኋላ እንዳይቀሩ ኩባንያችንም እንዳይጐዳ የህፃናት መዋያ ሠራን፡፡ እናት ልጇን እቤት ጥላ ብትወጣ ልቧ መሰቀሉ አይቀርም፡፡ አሁን ግን ልጇን አጠገቧ ባለ የህፃናት ማቆያ አስቀምጣ፤ ወጣ እያለች እያጠባችና እየጐበኘች ሥራዋን ትሠራለች፡፡ ተጠቀምን እንጂ አልተጐዳንም፡፡ እኔ በግሌ ለሴቶችና ለእናቶች አዳላለሁ፡፡ የእነሱ የበላይነት የሚረጋገጥበት ዘመን እስኪመጣም ማዳላቱን እቀጥላለሁ፡፡›› ብለዋል፡፡

## ይናገራል ፊቴ

እናት አለም አንቺ የፍቅር አስተማሪ
አካልሽ በሙሉ የፍቅር ዘካሪ
ውድድ የማረግሽ ስስት የምልልሽ
ውድዬ ውዲቱ እማምዬ አንቺ ነሽ
እናቴ ፍቅርዬ ወዳጄ የልቤ
ብዙ አመት ባንቺ ላይ የጣልኩት ሀሳቤ
ለጄ ይህ ይበጃል ይህ ይሻላል ብለሽ
እድሜዬ ቢገፋም ያው ነው እሹሩሩሽ
እረ እማማ ያንቺስ ከማንስ ይገጥማል
አረሳም አለብኝ ሆዴ ይሸበራል
እማማ ወልደሽኝ አሳደግሽኝ በፍቅር
ምንም ሳይጎልብኝ አርገሽ ሽቅርቅር
ቢከፋሽ ቻል አርገሽ ስቀሽልኝ ለኔ
ትይኝ የነበረ ወርቅና ብርሀኔ
እማማ ዛሬማ ገባሽ ከአንጀቴ
ሲናፍቅሽ ያድራል መላው አከላቴ
እናቴን አርግዝ ሽሉ ይላወሳል
ሳምጣት ሳምጣት አንጀቴ ተላውሶዋል
ወድሻለው እማ ከልብ ከአንጀቴ
እስቲ እይ እማምዬ ይናገራል ፊቴ

*ፅድላዊት*

## የእናት ውለታዋ

የበዛ ነው እጂግ የእናት ውለታዋ!
ተርባ ተጠምታ ደብቃ ጉያዋ
ፍትፍት ታጎርሳለች እናት ወለላዋ::
ፍትፍት ታጎርሳለች እናት ወለላዋ::
ሠውነቴ ሲሞቅ ሲያተኩሥ ገላዬ
ከራሴ ጀምራ የምትዳሥሰኝ የማር-ወለላዬ
እናቴ ብቻ ነች መጠጊያ ጓዳዬ::
እናቴ ብቻ ነች የኔ መጠጊያዬ::
ክፉሽን እንዳላይ ሥቃይሽን ሁሉ
የአምላክ ቸርነቱ የምሕረት ቃሉ
ሑሌም አይለይሽ ይደርብሽ በአንች
አይንካሽ ትካዜ ኑሪ ሳትሞች::
አይንካሽ ትካዜ ኑሪ ሳትሞች::
ችግር ሲበዛብኝ ርኃብ ሲጠና
ወይ! ዕናቴ ድረሽ ብዬ አሥብሽና
እጠግባለሁ በአንቺ ከረኃብ ቀጣና::
እርጅናው ቢጫንሽ ጣትሽንም ቢያጥረው
እናቴ ኑሪልኝ እጅሽ መኃሪ ነው::

*...ፍ...ታ... ዕ...ወ ...*

## ደግሠዉ አንቺ ነሽ

የእኔነቴ ተሥፋ ለዉስጤም ርካታ
ጣቶችሽ በረከት ክንዶችሽ መከታ
የአንገቴ-መኃለቅ የደስታዬ አለኝታ
የተፈጥሮ-ዋሻ የገነት-ኮረብታ
የረድዔት ሥሪት የትህትና ጎታ
ደግሠው አንቺ ነሽ ያኑርልኝ ጌታ::
ሕይወቴ እንዲሰምር እንዲያምር ጂምሩ
ደፋ ቀና ብለሽ ሁሉን አሳልፈሽ እንደዬ ምግባሩ
ለዛሬዉ ሕይወቴ ሥኬቱ ሚስጥሩ
ደግ ሰው አንቺ ነሽ መልካም-ስመ_ጥሩ::
በሥደትም ብኖር ከአንቺ ተለይቼ
ከአጠገብሽ ባልኖር ባላይሽ በዓይኖቼ
ሁሌም ከጎንሽ ነኝ መንፈሴን አፅንቼ::
ምንም እንኳ ባልችል ባይረዳኝም አቅሜ
ችግርሽን ባልቀርፈዉ በችግርሽ ቆሜ
ከእናትነት ሚስጢር ከየዋሁ ልብሽ
ተሥፋን ና ፍቅርን ደግነት ተሞልተሽ
ተርበሽ ....ተጠምተሽ....እንዳይሆኑት ሆነሽ
ለዚህ ለአበቃሽኝ በምክርሽ አንፀሽ
ይድረሥ ምስጋናዬ ደግሠዉ አንቺ ነሽ::

*ምንጩ ያልታወቀ*

**‹‹ፈጣሪ ሲፈጥረን ለሴቶች አዳልቷል:: ሴሎች ሴላ ሊሉት ይችላሉ፤ እኔ ግን ቁምነገረኝነታቸውን አውቆ መውለድ ለሚሉት ታላቅ ጸጋ መረጣቸው ነው የምለው...››**

*ዶ/ር አረጋ ይርዳው*

# የእናት ቀን መቼ ተጀመረ?

**ዘመናዊው የእናቶች ቀን የተከበረው በ1908 እ.ኤ.አ. አና ጃርቪስ የተባለች ሴት እናቷን ለመዘከር ባዘጋጀችው ዝግጅት ነው። ከዛም የእናቶች ቀን በአሜሪካ እንዲታውቅ እና እንዲከበር የተለያዩ ቅስቀሳዎችን ማድረግ ጀመረች። ከ6 ዓመታት በኋላ ውጤቱ ሰምርሳት በዓሉ በሀገራዊ ደረጃ መከበር ጀመረ**

እናት ጥልቅ ነው፣ እናትነት ውስብስብ ነው፣ እናትነት ታላቅ ሚስጥር ነው፡፡

እናት ሀገር ናት፣ እናት ማረፊያ ናት፣ እናት መምህር ናት፣ እናት ወዳጅ ናት፣... እናት ሁሉንም ነች። ምክንያቱም ልጆችን የማሳደግ፣ የመንከባከብ፣ ሥርዓትና ባህልን የማስያዝ፣ ከፍተኛ ቀንበር ይበልጡኑ በእናት ጫንቃ ላይ ሰለሚወድቅ ነው፡፡

እናት የጥንካሬ ምልክት ናት ብዙ ውጣ ውረድና ብዙ መከራና ስቃይ ውስጥ ታልፋለችና።

# ክብር እና ፍቅር ለእናቶች

# ሁሉ!




*በነፃ የሚታደል (Distributed at no Cost)*